# የሕዝብ ኑሮ፡
# በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና በኢትዮጵያ መሬት ላይ
## ክፍል ሁለት

**ፍስሐ ዘማርያም - ታህሣሥ 21/2002**

***ማገጣጠሚያ***

በክፍል አንድ እንደተገለጸው፤ የዚህ ጽሁፍ ዋና ጉዳይ የአብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ የመሬት ላይ "የሲያል" ኑሮና የቴሌቪዥን ላይ "የገነት" ኑሮ በንጽጽር ማየት ነው። ንጽጽሩ የፕሮፓጋንዳውን ዓይን ማውጣትና ጎን ለጎንም የሕዝቡን የኑሮ ችግር ጥልቀት እንዲሁም አንገብጋቢነቱን በይበልጥ ለመገንዘብ ይጠቅም ይሆናል፡፡ ኑሮአቸው በእጅጉ ተሻሻለ የተባሉ ጥቂት ሰዎች እንዲሁም የቁጥር መስፈሪያ የማያውቃቸውና በመሬት ላይ የማናያቸው ሌሎች መናፍስትም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ነጋ ጠባ ይቀርቡልናል። በክፍል አንድ፤ የፕሮፓጋንዳው ባህርይ፤ ተልእኮ፤ ዓላማ፤ ይዘትና አቀራረብ ተዳሷል። በዚህ በክፍል ሁለት ደግሞ በኢቴቪ ከሚቀርብልን የምናባዊ ፍጡራን "የድሎትና የምቾት ኑሮ" በተቃራኒው ያለውን ዕውነታ እናያለን። ስለራሳችን ስለተራ ሰዎች ማለትም ሥጋና ነፍስ ስላለን ግለሰቦች፤ ስለቤተሰቦቻችን፤ ስለጎረቤቶቻችን፤ ስለሥራ ባልደረቦቻችንና ስለ ወገኖቻችን በመሬት ላይ የሚታየውን በመከራ የተሞላ የዕለት ኑሮ፤ ቦታ፤ ጊዜና ሁኔታዎችን እያጣቀስን እኛው ራሳችን እንናገራለን - እንነጋገራለን። ይህንንም ሳናወሳስበው በራሳችን በተራ ሰዎች የዕለት በለት ቋንቋ ለመግለጽ እንሞክራለን።

በዚህ ክፍል የሚቀርበው ጽሁፍ የመደበኛ (የመስክ፤ የቤተመጻህፍት) ምርምር ውጤት አይደለም። በዋነኛነት (ከነጉድለቱም ቢሆን) አቅም የፈቀደውን ያህል ረዘም ላለ ጊዜ የተደረገ የምር አስተውሎትና ማሰላሰል ውጤት ነው። ጥቂት ከማይባሉ ባለጉዳዮች ጋር በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ የምር ውይይቶች ለጽሁፉ ትልቅ አስተዋጽዖ አድርገዋል። አንዳንዱን መደምደሚያዬን ደፋር ሆኖ የሚያገኘው አንባቢ በራሱ መረጃና ማስረጃ ያስተካክለው። እኔ ግን የማየው እንደዛው ነውና ከመግለጽ ሌላ አማራጭ አላገኘሁም። የንዴት ስሜት ያዘሉ አቀራረቦችም ከበዙ ከፊሎቹን ልደብቃቸው ስላልቻልኩ ነው፤ ከፊሎቹ ግን ከእርማት ያመለጡ መሆን አለባቸው። ለሁሉም ይቅርታ!

የኢኮኖሚ ዕድገትና ውድቀት ትንታኔውን፤ ቁጥሩንና ቴክኒካዊ ቋንቋውን ባለሙያዎቹ ይሉታል። በኢኮኖሚ መጻህፍት፤ የጥናት ወረቀቶችና የፖሊሲ ሠነዶች ላይ የሚቀርቡት ዓይነት ምሁራዊ ክርክሮችና ዝርዝሮችም እዚህ አይገኙም። እዚህ የሚቀርቡት የአስከፊው ኑሮአችን ልዩ ልዩ ማሣያዎች ናቸው። እዚህ ያልተገለጹ የአስከፊው ኑሮአችን ማሣያዎች እንደሚበዙና እንደሚከፉም እርግጥ ነው። ሌሎች ዜጎችና ሕዝባዊ ምሁራን በሚያደርጉት የተሻለ አስተዋጽዖ ይበልጥ ሥጋና ነፍስ ያላቸው፤ የተለያዩና ሁሉን አቀፍ የሆኑ የኑሮአችን ማሳያዎችን እናገኛለን። እነዚህን ከነመንስኤና የመፍትሔ ሐሳባቸው ለውይይት በማቅረብና በማዳበርና ለህዝባዊ ትግሉ ግብዓት ማድረግ ነው ትልቁ ነገር። የንጽጽሩን የተሟላ ሥዕልና መልእክት ማየት እንዲቻል፤ የዚህ ጽሁፍ ክፍል አንድ በቅድሚያ ወይም ከዚህ በኋላም ቢነበብ ጥሩ ነው። ዛሬ በኢትዮጵያ በመሬት ላይ የሚታየው የታችኛውና የመካከለኛው መደብ የከተማ ሕብረተሰብ የዕለት ኑሮ ከብዙ በጥቂቱ የሚከተለውን ይመስላል።

## የሕዝብ ኑሮ በኢትዮጵያ መሬት ላይ - በእኛው ዓይን!

### በቆሎ፤ ድንችና ጎመን ላይ መድረስ ከባድ ነው

አብዛኛው ሕዝብ የጤፍ እንጀራ፤ የስንዴ ዳቦ፤ የገብስ ቆሎ፤ የዘይትና የበርበሬ ሹሮ ወጥ ለዓመት በዓል እንኳን ብርቅ ሆኖበታል። ለወትሮ ቀለል ባለ ዋጋ ይገኙ የነበሩ እንደ በቆሎ፤ ድንችና ጎመን የመሰሉ ምግቦችም የአዘቦት ምግብነታቸው በጣም እየቀነሰ ነው። አብዛኛው ሕዝብ በቀን ሦስት ጊዜ የነፍስ ማቆያ እነሱን እንኳን መቅመስ የማይችልበት ደረጃ ደርሷል። በዚህ ምትክ የቤተሰብ አባላት (ወላጆችን ተዉና ልጆቻቸው) ምሣና እራትን በፈረቃ መቃመስ ግድ ሆኖባቸዋል። በርካታ ተማሪዎች ምግብ ሳይቀምሱ ወደ ትምህርት ቤት መሄዳቸው የተለመደ ነው። ይህንን ወደታች በዝርዝር እንመለስበታለን።

መደበኛ ምግብና ቡና ቤቶችን ተሰናብቶ መደበኛ ያልሆኑ የሜዳ ላይ ምግብና ሻይ መሸጫዎች ደምበኛ የሆነው ተጠቃሚ ቁጥሩ በጣም ጨምሮአል። መደበኛ ያልሆነ የልባሽ ጨርቆችና የቤት ዕቃዎች ንግድም በየጎዳናውና በየጥጋጥጉ ተስፋፍቷል። የነዚህ አገልግሎቶች አብዛኛው ተጠቃሚም የወትሮው ሣይሆን አዲስ ደንበኛ ነው። የጎዳና ምግብ ቤቶች አዲሶቹ ደምበኞች ማናቸው? ቀደም ብለው ከነበሩበት የተሻለ የኑሮ ደረጃ (ከዝቅተኛው የመካከለኛ መደብ) በኑሮ ውድነቱ ተገፍትረው ወደ ዝቅተኛው መደብ የወረዱና ወደዚህ የመጡ ናቸው። ዕውነቱ ከኢቴቪ አደንቋሪና አናዳጅ ፕሮፓጋንዳ ፍጹም ተቃራኒ ነው። “እድሜ ለአብዮታዊ ዴሞክራሲ መሥመራችንና ለፈጣኑ የኢኮኖሚ ዕድገታችን፤ ብዙ ሕዝብ ከዝቅተኛ መደብ ወደ መካከለኛ መደብ አድጓል” ይለናል ኢቴቪ - ያለአንዳች ሐፍረት። በነገራችን ላይ አዲሶቹም ደንበኞች ቢሆኑ በጎዳና ምግብ ማቅረቢያዎች መስተናገድ የቻሉት ሥፍራው በሽግሽግ ተለቆላቸው ነው። የጎዳና ተዳዳሪዎች፤ የቀን የጉልበት ሥራ ሠራተኞች፤ ሊስትሮዎች፤ ሲጃራ፤ ሎተሪ፤ ቆሎና ሶፍት አዟሪዎች ወዘተ፤ እነዚህ ነበሩ የቀድሞ የጎዳና ምግብ ቤቶች የታወቁ ደንበኞች። ዛሬ በዚያ ሥፍራ የሉም። በጎዳና ላይ፤ በአውቶቡስ መናኸሪያዎች ጥግ፤ በመግቢያና መውጫ በሮች ላይ፤ በዛፎች ጥላና በቆንጥሮች ሥር ይቀርቡ የነበሩት የተቀቀለ ድንችና በቆሎ፤ ቂጣ በጎመን፤ ቂጣ በአቦካቶ ወይም በሙዝ፤ ዳቦና ፓስቲ በሻይ፤ ሽንኮራ፤ የባቄላ አሹቅና ቆሎ ወዘተ ነበሩ። በወትሮ ሥፍራቸው ለወትሮ ደንበኞቻቸው እየቀረቡ አይደለም። ዛሬ ግን በነርሱ ምትክ በላስቲክ ጥላ ሥር በአግዳሚ መቀመጫዎች ላይ የሚስተናገዱት አዲሶቹ ግፉአን ደንበኞች፤ በየቢሮው የሚሠሩ የበታች ሠራተኞችና አነስተኛ ገቢ ያላቸው ወንደላጤዎች ናቸው። እነዚያ የቀድሞዎቹ ግፉአን ደንበኞች ከዚህም ተገፍትረውና ተወርውረው ምን ዓይነት የኑሮ አዘቅት ውስጥ ሊገኙ እንደሚችሉ ገምቱ።

በአዲስ አበባ መርካቶ ጥጋጥጎች ከምግብ ቤቶች በትርፍራፊነት የተሰበሰበ ምግብ **በጉርሻ ደረጃ** መሸጥ ከተጀመረ ሰነበተ። ግማሽ ወይም ስስ እንጀራ አይደለም እየተባለ ያለው። በመርካቶ **አንድ - ሁለት ጉርሻ እንጀራ ይሸጣል** ነው እያልን ያለነው። ከግፉአንም ግፉአን የሆኑ ዜጎቻችን፤ አንድአንድ የእንጀራ ጉርሻ (መካከለኛ ወይም ትልልቅ) በሳንቲም ቤት ገንዘብ እየከፈሉ በሰልፍ ተራ ገብተው እየጎረሱ ያልፋሉ፤ እናም በዚሁ ይውላሉ / ያድራሉ። እናም በረሀብ የተጎዳ አንጀታቸውን አስረው በመስጊድና ቤተክርስቲያኖች አጥር ሥር፤ በመቃብር ሥፍራዎች፤ በከተማ ፍሳሽ ውኃ መውረጃ ቱቦዎች ውስጥ፤ የተሻሉት ደግሞ በአውቶቡስ ፌርማታና በረንዳ፤ እንዲሁም በጋራ የኪራይ ማደሪያዎች ውስጥ ፈስሰው ሌሊቱን ያሳልፋሉ። የላስቲክና የካርቱን “ቤቶችም” በዚህ ዝርዝር ውስጥ አሉ። ሥራ ወይም ገበያ ስለሌለ የግዢ ጉርሻም እንኳን ሳይቀምሱ ጦማቸውን ለመዋልና ለማደር የሚገደዱትም መሰል ዜጎች ሥፍር ቁጥር የላቸውም።

ከኑሮው ትግል ገና ጨርሰው ተገፍትረው ያልወደቁ በመጠኑ ሻል ያሉት ደግሞ እንዲህ ያደርጋሉ። እንደወትሮው ለዓመት በዓል በግና ወይም የበሬ ቅርጫ ሥጋ በቤተሰብ ደረጃ መግዛት ቅንጦት ሆኖባቸዋል። የደሞዝ ሰሞንም ኪሎ ሥጋ በግል መግዛት እንዲሁ። ስለዚህ በጎረቤት ደረጃ ለሁለትና ለሦስት አንድ ኪሎ ሥጋ በቅርጫ “ማስገባት”ን እየተለማመዱ ናቸው። ሰው አየኝ አላየኝ በማለት እየተሸማቀቁም ቢሆን ሩብ ኪሎ ወይም ቅንጥብጣቢና እንደነገሩ የሆነ ሥጋ መግዛት መቻልም “መታደል“ ሆኖአል። ወተትና ዕንቁላልማ ሰፊው ሕዝብ ጋ በየት በኩል ደርሰው። አቅርቦትና ፍጆታቸው በሥዕል ደረጃ ሆኖአል። በጤና ጣቢያ የጤና ማስተማሪያ ሥዕሎች (ቻርትና ፖስተሮች) እና በንግድ ማስታወቂያዎች ላይ ይገኛሉ። ያሳዝናል!!

## በግልጽ የማይታዩ አሳዛኝ የኑሮ ገጽታዎች

ሌሎችም በቀላሉ ሊታዩ የማይቻሉ አሳዛኝ የኑሮ ገጽታዎች አሉ። በወፍጮ ቤት ጤፍ ሲበጠር በንፋስ የሚንገዋለለው ብጣሪና ትርፍራፊው ለብቻው ይሰበሰባል። እናም ወደ ሌላ አካባቢ ተወስዶ ለድሃው ከተሜ እንዳቅሙ ይሸጥለትና እርሱም “ጤፍ” በልቶ ያድራል። ትንሽ ንጹህ ጤፍ ገዝቶ ያንን ለማበራከት በዋጋ ረከስ የሚሉትን ማሽላና በቆሎ ቀላቅሎ የሚያስፈጨው የሕብረተሰብ ክፍልም በጣም ብዙ ነው። የድህነቱ መክፋት ከወፍጮ ቤቶች ጋር የተያያዘ ስርቆሽና የሚስጥር ገበያዎችንም መፍጠር ጀምሯል። እንደነገሩ የሞላላቸው አስፈጪዎች የሚያመጡት ድቁስ በርበሬ ከተፈጨ በኋላ የባለቤቶቹ መዘናጋት ታይቶ ከፊሉ በዘዴ እዚያው በወፍጮው ቋት ውስጥ ተቀንሦ ይቀራል። በኋላ ላይ በደንበኝነት የሚታወቁ የጉልት ነጋዴዎች በአነስተኛ ዋጋ በሚስጥር ይረከቡታል። እናም ኑሮ እያንገዳገዳቸው ያሉ ወገኖች በማይታመን ቅናሽ ዋጋ ከነዚህ ጉልቶች ገዝተው ቤታቸው ያስገቡታል።

በግንባታ ፕሮጀክቶች ውስጥ በጉልበት ሥራ ላይ የተሰማሩ የቀን ሠራተኞች፣ በጣም ትናንሽ የሆኑ የንግድ ሥራዎች የሚሠሩ፣ በተመላላሽነት በሦስት አራት ሰው ቤት ተቀጥረው የሚሰሩና በሌሎች መሰል ሥራዎች ላይ የተሠማሩ በአብዛኛው ሴት እህቶቻችንን እንውሰድ:: ኑሮአችሁ እንዴት ነው? ምኑን ከምኑና እንዴትስ ታብቃቁታላችሁ? በሉና የነሱ ሰው ሆናችሁ፣ በሐቀኛ ተቆርቋሪነት መንፈስ ቀርባችሁ ጠይቋቸው:: ለምሳሌ ማገዶ ከየት በስንት ያገኛሉ? አንድ ጆንያ ከሰል እንደሆነ ዋጋው ከ80 እስከ 110 ብር ስለሆነ ለነዚህ ወገኖቻችን (በችርቻሮ ደረጃም ቢሆን) የማይታሰብ ነው:: ነገር ግን እነርሱም "ከሰል" ገዝተው ምግባቸውን (በቆሎና ጎመናቸውን) እንደሚያበስሉ ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው እያመነቱ ይነግሯችኋል:: የነርሱ "ከሰል" ምንጩ የት ነው? በአብዛኛው ከምግብና ሻይ ቤቶች ምድጃ ውስጥ ታፍሶ የሚወጣው የአመድ ጥራጊና የልዩ ልዩ ደረቅ ቆሻሻዎች ጥራጊ ነው:: ይህ በቆሻሻ አንሺዎች ተሰብስቦ በከተሞች ዳርቻ ወደሚገኙ የቆሻሻ መጣያዎች ይራገፋል:: ከነዚህ ሥፍራዎች ላይ ለድሆች ማገዶ ሊሆን የሚችለውን ለይተውና በብዛት ሰብስበው በጉልት ገበያ ላይ በርካሽ ዋጋ ለሽያጭ የሚያቀርቡ ሌሎች ወገኖች አሉ:: በዚህ መንገድ የተገኘውንና ከጉልት የገዙትን "ከሰል"፣ ገና ስናያይዘው ትንሽ ሽታው ያስቸግረናል እንጂ ምንም አይልም ይሏችኋል::

ሕጻናት ልጆች ያሉት ድሀ ቤተሰብ ግን ይህን ማገዶ መግዛት ሳያስፈልገው ለራሱ አገልግሎት ከምንጩ ያገኘዋል:: የተቀዳደደ  ከረጢት ይዘው በየመንገዱ፣ በየመንደራችሁ፣ በየቤታችሁና ንግድ ቤቶች ደጃፍ ለማገዶ ለቀማ የሚንከራተቱትን የተጎሳቆሉ ሕጻናት አስታወሳችኋቸው? የጫት እንጨትም ዝም ብሎ አይታለፍም:: ሲያነዱት የጪሱና የሽታው ነገር አይጣል ነው እንጂ! የሰፊው ሕዝብ የማገዶ አቅርቦት ዑደቱ ሥዕል ከብዙ በጥቂቱ ይሄን ይመስላል:: ልብ በሉ! የዚህን ሂደት ዑደቱን እንጂ ሌሎች አስከፊ (የጤና፣ የጽዳት፣ የስነልቡናና ማህበራዊ) ገጽታዎቹን አልተመለከትንም::

## ጎዳና የወጡ ጎልማሦችና አረጋውያን

በሌላ በኩል ይህንን አታካች የኑሮ ትግል ፈጽሞ መቋቋም ያቃተውና ቁጭ ብሎ በረሃብ እንዳይሞት የፈራው ሴትና ወንድ ጎልማሣና አረጋዊ እየተሸማቀቀም ቢሆን ወደ ጎዳና ወጥቷል - ለልመና:: የነዚህን ወገኖቻችንን ማንነትና ብዛት በቀላሉ ለመለየት ያስቸግራል:: ብዙዎቹን አንገታቸውን ደፍተውና ዓይናቸውን ሰብረው፣ የመንገድ ምሰሶና ዛፍ ተደግፈው ወይም አንድ ጥግ ቆመውና ተቀምጠው፣ ሰው የሚጠብቁ መስለው ታገኙ ኣቸዋላችሁ:: ግማሾቹ እናንተው ምን እንደሚፈልጉ አውቃችሁ ካልሰጣችኋቸው አፍ አውጥተው አይለምኗችሁም:: በገጻቸው ላይ ማመንታትና አንዳች የሚደበቁትና የሚሸሹት ነገር እንዳላቸው ለመገመት አይከብዳችሁም:: የሚደበቁትና የሚሸሹት ወዳጅ ዘመዶቻቸውን፣ ጎረቤቶቻቸውን ወይም የናንተኑ ዓይን ሊሆን ይችላል:: ይህ ነባሩን የኃይማኖት ሥፍራዎችና የመንገድ ልመና አይመለከትም:: ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአዲስ አበባና በሌሎች ትልልቅና መካከለኛ የኢትዮጵያ ከተሞች የተለመደ ነገር ግን ልብ የሚሰብር ትዕይንት ነው:: ዝርዝሩ ብዙ ነው::

የሞላውና ያማረው የቴሌቪዥን ላይ ኑሮ እንዲደብቅ የተፈለገው ይህንን የሰውነትን ክብር የሚያዋርድ አሳዛኝ የመሬት ላይ የሕዝብ ኑሮ ነው:: እናም ዞምቢዎቹ የኢቴቪ ጋዜጠኞች ዓይኔን ግንባር ያድርገው በማለት፣ የሚሊዮኖችን የመከራ ኑሮ ወደ ጎን ብለው፣ የጥቂቶቹን "ሥራ ፈጣሪ" ወጣቶችና "የገበሬ ሚሊዮኔሮች" የኢቴቪ ላይ የምቾት ኑሮ ዋነኛው የሐገሪቱ ሥዕል አድርገው ለማሳየት ላይ ታች ይላሉ::

## የማን ጥፋት ነው? እኛስ እንደ ወገን ምን ይሰማናል? ምንስ እያደረግን ነው?

ይህና ይህን የመሳሰለው ሁኔታ፣ ለተጠቂው ሰው ብቻ ሣይሆን ለማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡርና በተለይም ተጠቂው የሐገሬ ልጅ አካሌ-ወገኔ ነው ለሚል ሁሉ ውርደትና እንቅልፍ የሚነሳ ስቃይ ነው የሚሆንበት:: በተለይማ በሐገር ውስጥ ሆኖ ይህን ዘግናኝና አሳፋሪ (የቴሌቪዥንና የመሬት ላይ) የኑሮ ትርኢት፣ እጅግ በሚበዛው ጊዜና ሥፍራ በቀጥታ ለማየት መገደድና መቻል በራሱ አንድ ትልቅ ስቃይ ነው:: አንድ የጎደለ ትልቅ ነገር እንዳለ ስለሚሰማህ ዘወትር ይጨንቅሐል:: የአእምሮ ሰላምና የሕሊና ዕረፍት ይነሳሃል:: ሰላም ማለት የጥይት ጩኸት አለመስማት ብቻ ነው እንዴ? አንተ/አንቺ ያልተራቡና ያልታረዙ ልጆችህን በግል መኪና፣ በኮንትራት ትራንስፖርትና በታክሲ ወደ ትምህርት ቤት ታመላልሳለህ:: ወይም በመንገድና በህጻናት መዝናኛ ሥፍራዎች በማንሸራሸርና በማዝናናት ላይ ነህ/ሽ:: ይህ በራሱ ጥፋት አይደለም:: በፍጹም ሊሆንም

አይችልም። ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ሊደርስበትና ሊያገኘው የሚሻ አንድ የሕይወት ዓላማ ነው። ነገር ግን በዚህ ወቅትና ሥፍራ ትምህርት ቤት የመሄድ እና በመዝናኛ ሥፍራዎቹ አጠገብ የመድረስ እንኳን ዕድሉን የተነፈጉ፤ በከፊል ራቁታቸውን የሆኑና የተጎሳቆሉ ህጻናትን ሁኔታ ስታዩ (ከነልጆችህ/ሽ) ምን ይሰማሃል/ሻል? ለልጆቻችሁስ ምን ትሏቸዋላችሁ? እንደነዚህ ልጆች እንዳትሆኑ ከአሁኑ ጨዋ ብትሆኑና ትምህርታችሁን ጠንክራችሁ ብትማሩ ይሻላችኋል ነው የምትሏቸው? የእናንተ ልጆች ይህን ዕድል ያገኙት በራሳቸው ምርጫና ጥረት ነው? እናንተ ያቀረባችሁላቸው አይደለምን? እነዚያስ ህጻናት ያንን ዕድል ያጡት በራሳቸው ምርጫና ጥፋት ነውን? እነርሱስ እራሳቸው በሥርዓቱና በኛም ጭምር የመረሣት ሰለባ እይደሉምን? ይህንን የጥያቄ ሠንሰለት ቋጠሮውን ፈትቶ አጥጋቢ መልስ ለማግኘት መጣር በራሱ አታካችና ከንቱ ልፋት ይሆንብናል። ሃሳቡን ራሱን እርግፍ አድርገን ለመተውና ለመርሳት ማለትም ራሳችንን ከዕውነታው ለመደበቅና ለማምለጥ እንወስናለን። ችግሩ፤ አብዛኛውን ጊዜ ይህም በራሱ ከንቱ ልፋት ነው የሚሆንብን። ምክንያቱም ባለ 'ወፍራም ቆዳ' ካልሆንን በስተቀር ጤና አይሰጠንምና! ጤና ማለት የአካል አለመታመም ማለት ብቻ አይደለም። በተለይ በተለይማ ሁኔታውን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ለመለወጥ ትንሽም ቢሆን ራሱን ላልሰጠ (ለመስጠት ገና ላልወሰነ) ሰው፤ የጥፋተኝነት ስሜቱና የሕሊና ዕዳው አይጣል ነው! ከውጭ ነዋሪው ኢትዮጵያዊ አቅጣጫ ያለውን እይታ በቅጡ አላውቅም። ብንስማው ጥሩ ነው። ነገር ግን በዚህ ረገድ አንዳንዴ በአካል ርቆ ውጭ መኖር  በአንጻራዊነት የተሻለ የሕሊና እረፍት ሳያስገኝ አይቀርም።

ዞሮ ዞሮ ሁኔታውን ለመቀየር ምን እያደረግን ነው? ምንስ ማድረግ አለብን? በያለንበት አንድ ነገር በአንድነት ማድረግ እንዳለብን አይሰማችሁም? ለለውጥ መነሳት? የለውጡን እንቅስቃሴ በተለያየ ደረጃና መልክ መቀላቀል? እንደየዝንባሌያችንና እንደየአቅማችን ትግሉን ማገዝ? እኛ ይህን ትንሽ ነገር ግን ጠቃሚ እርምጃ ስንወስድ ቀድመው በሥራ ላይ ያሉት የለውጥ ኃይሎች ደግሞ በሁሉም ረገድ ይነቃቃሉ። በዚህ መንገድ የነጻነት ጊዜ ሁሌም እየራቀን መሄዱን ያቆማል።

## የተማሪዎቹ ሆድ ብቻ ሣይሆን አእምሯቸውም ምግብ አያገኝም: ሥርዐተ ትምህርቱም ባዶ ነው!

በኢትዮጵያ በበርካታ ቤተሰቦች ውስጥ፤ ልጆች ምሣና እራትን በፈረቃ መቃመስ ግድ እንደሆነባቸው በዚህ ክፍል መጀመሪያ አካባቢ ተገልጿል። በርካታ ተማሪዎች ምግብ ሳይቀምሱ ወደ ትምህርት ቤት መሄዳቸው የተለመደ ነው። የቁርስ ወይም የምሳ ተረኛ ያልሆኑት ምስኪን ተማሪዎች ሆዳቸው ባዶ በመሆኑ ምክንያት በክፍል ውስጥ አካልና አእምሯቸው ይከዳቸዋል። የኢትዮጵያን 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ አስተማሪዎች ጠይቋቸው። ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት ስለሚያንቀላፉና አንዳንዴም ተዝለፍልፈው ስለሚወድቁ ተማሪዎቻቸው ሁኔታና ብዛት የሚነግሯችሁ ነገር በዕውነት ያስደነግጣችኋል። እነዚህ ረሀብተኛ ልጆች ማንን እና ምኑን ነው የሚያዳምጡት? አስተማሪያቸውን ወይስ የሆዳቸውን ጩኸትና የሰውነታቸውን መዝለፍለፍ? አእምሯቸውስ በትክክል የሚሠራ ይመስላችኋል? በመሠረቱ ባዶ ሆዳቸውን ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱ ልጆች ለትምህርት ዝግጁ አይደሉም፤ ሊሆኑም አይችሉም። በዚህ አስከፊ ሁኔታ ውስጥ የሚማር ተማሪ የትምህርት ውጤቱና መጨረሻውስ ምንና የት ሊሆን ይችላል? ችግሩ ግን በዚህ ብቻ አያበቃም።

ሌላ ሌላውን ተዉትና ሥርዓተ ትምህርቱ ራሱ ባዶ ነው፤ የጥራት ረሀብ ያጠቃው ነው። በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ለለጋሾች ፍጆታ በሚዘጋጁ ወረቀቶች ላይ የምታዩት አንጸባራቂ የሆነ የትምህርት ክንዋኔና ስኬት መኖሩን ነው። "ዕድሜ ለአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲአችን፤ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች (public schools) የ1ኛ ደረጃን የትምህርት ሽፋን 80% አድርሰነዋል። በዓለም ደረጃ የተቀመጠልንን የሚሊኒየም የትምህርት ግብ ጊዜው (2015) ከመድረሱ በፊት ያለጥርጥር ልናሳካው ነው" ይሏችኋል። ስለዚህ አጨብጭቡልን ነው ነገሩ። እናጨብጭብ ይሆን? በመሠረቱ ቁጥሩ (80%) ራሱ ከባድ ችግር ያለበት ነው። በየትምህርት ዓመቱ (መስከረም) እና በየትምህርት ደረጃው (1ኛ ክፍል) መጀመሪያ ላይ የተመዘገበውንና በመሐልና በመጨረሻው ላይ በተጨባጭ የሚገኘውን የተማሪ ቁጥር አገናዝቦ ዕውነቱን ለማወቅና ለመግለጽ የሚፈልግ/የሚደፍር የለም። ለሪፖርት አይመችማ! ስለ ቁጥራቸውስ የተባለው ተባለ፤ የጥራቱስ ነገር? በተጨባጭ ግን ትምህርት ቤት የገቡት ልጆች በየደረጃው ምን ያህል አጥጋቢና ተገቢ ዕውቀት፤ ክህሎትና አመለካከት ይዘው ተገኙ? የትምህርት ዕድል መስጠት ማለት ልጆችን በአራት ግድግዳ መሀል አጉሮ ማዋል ማለት ነው እንዴ? እንደገና እንጠይቅና የጥራቱስ ነገር? ልጆቹ ትምህርት ላይ ናቸው ወይም 1ኛ ደረጃ

ጨርሰዋል ቢባሉም ሌላው ይቅርና **ማንበብና መጻፍ እንኳን በቅጡ አይችሉም እኮ!!** ይህ በፍጹም ማጋነን አይደለም። እኛ እዚህ የምናወራው እንደ ዜጋ፤ እንደ ጉዳዩ ባለቤትና እንደ ችግሩ ዋነኛ ገፈት ቀማሽ ነው። በሐሰት የተሞላ የሸፍጥ ፕሮፓጋንዳ አንገሽግሾናል። አሁንስ በዛ፤ በቃ ማለት በቃ ነው! የተሟላ ለውጥ እንፈልጋለን! አንድ ነገር ማድረግ አለብን! ብለን ነው። እንጂ የጠላነውን ራስ ወዳድ የሆነ የአንድ ፖለቲካን መሰሪ ፕሮፓጋንዳ በሌላ መሰል ዓላማ ባለው ፕሮፓጋንዳ ቀይረን እራሳችንን ማታለልና አሳራችንን ማራዘም አይደለም ፍላጎታችን። ችግሮችን በማዛባት፤ በማጋነንም ሆነ በማንኳሰስ ራሳችንን ለበለጠ ኪሳራ ከመዳረግ ውጭ ምንም ትርፍ እንደማናገኝ ጠንቅቀን እናውቃለን። እናም የጥራቱስ ነገር እያልን ደግመን ደጋግመን እንወተውታለን። በተለያዩ መድረኮች ላይ እንደሚደረገው፤ በአንድ ሐገር አቀፍ የትምህርት አውደ ጥናት ላይም የጥራቱስ ነገር? የሚል ጥያቄ ተነስቶ እንደነበር ይህ ጸሐፊ መረጃ አለው። ከስማቸው ፊት ቅጽል ያላቸው ሁለት ሦስት "ምሑራን" (ዞምቢዎች!) ሳይቀሩ ጥያቄውንና ጠያቂውን በማጣጣል ተንጫጩ። ጥያቄው የቀረበለት ተናጋሪ ግን እግዜር ይስጠውና እውነት ነው ያለውን መልስ ሰጠ። "በአሁኑ ጊዜ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት እየሰጠ ያለው እውነትም በትምህርቱ ጥራት ላይ ሳይሆን በሽፋን (በማዳረስ ላይ) ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት በ2015 ዕድሜያቸው የደረሰ ህጻናት ሁሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንዲያገኙ እናደርጋለን ብሎ መንግሥት በዓለም ፊት ቃል ስለገባና ይህንንም መፈጸም ስላለበት ነው" አለ ተናጋሪው። ይህ እንግዲህ ማንበብና መጻፍ በቅጡ የማይችሉ ተማሪዎችን እያመረትንና እያጨድን ያለነው ምንና እንዴት ስለዘራን እንደሆነ በግልጽ የሚያሳይ ይመስለኛል።

በዚህ መንፈስ ለምሳሌ በመንግሥት ትምህርት ቤት 6ኛ ክፍልና ከፍ ያለ ክፍያ በሚጠይቅ የግል ትምህርት ቤት 1ኛ ክፍል የሚማሩ ሁለት ተማሪዎችን (ሁለቱም አማካይ ተማሪዎች) የዕውቀት፤ የችሎታና የአመለካከት ደረጃ አነጻጽሩ። ተነጻጻሪዎቹ ተማሪዎች በየክፍል ደረጃቸው የወሰዱት መደበኛ ትምህርት ባስገኘላቸው/ባላስገኘ ላቸው ብቃት ወይም አፈጻጸም ረገድ በመሀላቸው የምታዩት ልዩነት አስደንጋጭ ነው። ይህ በአጭሩ ተገቢም ፍትሐዊም አይደለም። አንድ የተበላሸ ነገር ስለመኖሩም ለመገመት አያዳግትም። እርግጥ ትምህርት በየትም ዓለም የመደብ ባህርይ አለው። በአጠቃላይ አነጋገር የሐብታምና የድሀ ልጅ በትምህርትም በብቃትም እኩል ዕድል አያገኙም። ዕውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ታዲያ አሁን እዚህ ምኑ ነው አዲስና አስደንጋጭ ሆኖ የተገኘው? ብለው የሚከራከሩ አይጠፉም። አስደንጋጩ ነገር የሚገኘውና የሚታየው ጉዳዩን በመጽሀፍና በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ሲተነትኑት አይደለም። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ በየደረጃው ያለውን የመንግሥት ተማሪዎች (የምሩቃኑን ሳይቀር) የአፈጻጸም ብቃት ከግል ተማሪዎች አኳያ ብቻ ሣይሆን በዚያ ደረጃ ከሚጠበቀው ዝቅተኛ ተፈላጊ ብቃት አኳያ በተጨባጭ ገመግሙት (reality check የሚሉትን ሥሩ ለማለት ነው)። ያኔ ነው ከአስፈሪው ዕውነታና ሐገራዊ ኪሣራ ጋር የምትፋጠጡት። የሚጠበቀውና በተጨባጭ የሚታየው የተማሪዎቻችን የአፈጻጸም ብቃት ደረጃ ልዩነቱ የሰማይና የመሬት ያህል የተራራቀ ነው። ከዚህ በላይ ዝርዝር ውስጥ መግባት የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ስላልሆነ በዚሁ ልንተወው ነው።

በአጭሩ ግን የተማሪዎቻችን ሆድ ብቻ ሣይሆን አእምሯቸውም የሚፈልገውንና የሚያስፈልገውን ምግብ እያገኘ አይደለም፤ ምክንያቱም ሥርዐተ ትምህርቱም ባዶ ነውና! በተለይ ትንንሾቹ ልጆቻችን ድምፅ - የለሽ ናቸው። ግን ማን ነው ልጆቹን ሆኖ ወይም የልጆቹ፤ የትውልድና የሐገር ጉዳይ ነው ብሎ ይሄንን የሚጠይቅላቸው? ይህ ለነርሱ አይገባቸውም የሚልላቸው ማን ነው? "ለጋሾቹ" እንደሆን በመሠረቱ አበረታች ክንዋኔ አሳይታችኋል፤ በተጨማሪ ይህችንም ጉዳይ ብታጤኗት ነው የሚሏቸው፤ ሰዎቹን። ከዚህ የተለየ ለማለት መረጃው ቢኖራቸውም ፍላጎትና ድፍረቱ ከየት መጥቶ! በዚህ ሁኔታ (ቀድሞ በጸረ ሽብር አሁን ደግሞ በአየር ንብረት ረገድ) አጋር ለሆነ መንግሥት የሚሰጡት ምላሽ ከፍተኛ ጥንቃቄ የተሞላበት ነው። ገንዘባችንን በአግባቡ ካልተጠቀማችሁበት ብሎ የምር ለመቆጣትና እርምጃ ለመውሰድ ሆዳቸው (ብሔራዊ ጥቅማቸው) እሺ አይላቸውም።

## ***የመሠረታዊ ትምህርት ዕድል የት ገባ?***

ድህነት ትምህርት ቤት የመሄድ ዕድል መነፈግ እናም ማንበብና መጻፍ አለመቻል መሆኑንም በክፍል አንድ አውስተን ነበር። በኢትዮጵያ በተንሰራፋው ድህነትና ተያያዥ ምክንያቶች ዕድሜው ለ1ኛ ደረጃ ትምህርት ቢደርስም ትምህርት ቤት እስከነአካቴው የማይሄደውን ቤቱና ጎዳናው ይቁጠረው። ትምህርቱን ለማቋረጥ ተገዶ ወደ ፍጹም መሐይምነት የሚመለሰውም ልጅ፤ ወጣትና ጎልማሳ ቁጥሩ ቀላል አይደለም። ለነዚህና ዕድሜአቸው

ከገፋም በኋላ መሠረታዊ ትምህርት ለማግኘት ላልታደሉ ዜጎች የሚቀርብ ይህ ነው የሚባል የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መርሐ ግብር (Alternative Basic Education) የለም ማለት ይቀላል:: ስለዚህ በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ማንበብና መጻፍ የማይችለው ዜጋ ቁጥር ከፍተኛ ነው:: በዚህ ረገድ እንዲያውም በደርግ ጊዜ ይታይ የነበረው ጥረት በእጅጉ የተሻለ ነበር ማለት ይቻላል:: ዛሬ በሰከነ አእምሮ ሚዛናዊ ሆነን እናጢነው:: አምባገነኑ የደርግ መንግሥት በዓለም ፊት ከተመሰገነባቸውና መንግሥቱ ኃይለማርያምንም በዚምባብዌ ስደት ላይ እያለ እንኳን ለሽልማትም ካበቁት ጥቂት አመርቂ ክንውኖች መሀል አንዱ በመሠረተ ትምህርት ረገድ ያስመዘገበው ነው:: ታዲያ ይህ የኋልዮሽ ጉዞ ከየት መጣ?

ኢሕአዴግ መንግሥት ከሆነበት ቀን አንስቶ ፍጹም ትኩረት ከነፈጋቸው የትምህርት ጉዳዮች መሀል አንደኛው ይኸው መደበኛ ያልሆነ ትምህርት (Non Formal Education) ነው:: (ምናልባት ደርግን ስለሚጠላ ይሆን ይህን ያደረገው?) ሁለት ዓሠርት በሚጠጋው የሥልጣን ዘመኑ በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አገልግሎት ረገድ የተፈጠረውን ሰፊ ጉድለት ማጤን የጀመረው ገና ከሦስትና አራት ዓመት ወዲህ ነው:: ያውም በእርዳታ ሰጪዎች ግፊት! እንደዚያም ሆኖ እስካሁን የተጨበጠ ለውጥ አልታየም::

መሐይምነትን በመዋጋት ረገድ የታየውን ፍጹም ንዝህላልነት የሚገልጸው ከሆነ፤ አንድ የሚያሳፍር ገጠመኝ ላካፍላችሁ:: ነገሩ የሆነው ከአንድ ሁለት ዓመት በፊት ነው:: ትልቅ አውደ ጥናትና የምክክር መድረክ ከአዲስ አበባ ውጭ በአንድ ትንሽ ከተማ ተዘጋጅቷል:: ዓላማው በሐገር አቀፍ ደረጃ እንዲጀመር ለታቀደው መደበኛ ያልሆነ ትምህርት (የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት) መርሐ ግብር ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ነው:: በስብሰባው ላይ የትምህርት ምክትል ሚኒስትሩ፤ የሁሉም ክልሎች ትምህርት ቢሮ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፤ ጉዳዩ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ኃላፊዎችና የትምህርት ባለሙያዎች ተገኝተዋል:: የጥናት ጽሁፍ ካቀረቡት መካከል አንድ ኡጋንዳዊ የጎልማሦች ትምህርት ባለሙያ ይገኛል:: ኡጋንዳዊው ንግግሩን የደመደመው ተሰብሳቢውን ሁሉ ባሸማቀቀና አንገት ባስደፋ የእጅ አዙር ወቀሳ ነው:: ቃል በቃል ባይሆንም:

> *በኡጋንዳ መደበኛ ያልሆነ ትምህርት (መሠረተ ትምህርት) መርሐ ግብር "ሀ" ብለን የጀመርነው ከሠላሳ ዓመት በፊት ነው:: ያኔ ምንም ልምድ አልነበረንም:: ኡጋንዳን መደበኛ ያልሆነ ትምህርት (Non Formal Education) ያስተማራት አውሮፓዊ ወይም አሜሪካዊ አይደለም::* ***ኢትዮጵያዊ*** *ባለሙያ ነው!! ያ ሰው ዛሬ እዚህ ከፊት ለፊቴ ተቀምጧል* (ባለሙያውን ስሙን ጠርቶ እያመለከተ)*:: የኔን የቀድሞ ተማሪውን ገለጻ እያዳመጠ ማስታወሻ ሲወስድ እየተመለከትኩት ነበር:: እኔ እሱን* (ልብ አድርጉ! ኢትዮጵያን እንደ ማለት ነው) *"ሳስተምር" አልተመቸኝም:: ይህን እናንተ እንዴት እንደምትመለከቱት አላውቅም:: ለኔ ግን እያስጨነቀኝ ነበር:: ግራ የሚያጋባ ነገር ነው የሆነብኝ:: አስቡበት::* አለ በትህትና::

## የኢኮኖሚ ለውጡና ድህነትን ማስወገድ

እንግዲህ ረሀብና እርዛቱ፤ መጠለያ አልባነቱ፤ መሐይምነቱ ወዘተ የህጻናት፤ የወጣቶች፤ የጎልማሦችና የአረጋውያን፤ የወንዶችና የሴቶች በአጠቃላይ የዜጎች የአዘቦት ሰቆቃ በሆነበት ሐገር ነው ያለነው:: ይህ አስከፊ ትእይንት የሚታየው፤ የዜጎቹን መሠረታዊ የሆኑ የኢኮኖሚና ማህበራዊ መብቶች እንዲያሟላ የሚጠበቅበት መንግሥት የሚባል ተቋም ባለበት ሐገር ነው:: የኢኮኖሚና ማህበራዊ መብቶችን በሕገመንግሥቱ ወረቀት ላይ አስፍሮና ተዛማጅ ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችንም ተቀብያለሁ ስለሆነም ለማሟላት የታቀደ ጥረት አደርጋለሁ ብሎ ቃል የገባ መንግሥት ባለበት ሐገር ነው:: ይህ ብቻም አይደለም:: በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት (የማን መንግሥት ነው?)፤ የበለጸጉ ሐገሮችን ሳይቀር የሚያስንቅና የሚያስቀና ባለ ሁለት አሀዝ የኢኮኖሚ እድገት ለተከታታይ ዓመታት አስመዝግቤያለሁ እያለ ጉራ ሲነዛና ያለሀፍረት ጮቤ ሲረግጥም የምንታዘብበት ሐገር ነው::

በዚህ ሐገር በእርግጥ የኢኮኖሚ ለውጥ አለ:: መንገዶች፤ ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች ተገንብተዋል:: ቁጥራቸው የበዛ ህጻናትና ወጣቶች ወደ ትምህርት ቤት መሄድ ችለዋል:: የትምህርቱ ጥራት ጉዳይ ሳይነሳ:: ኢሕአዴግ በትምህርት ዘርፍ ፊቱን ወደ ጥራት ጉዳዮች ለመመለስ የምር ጥረቶች ሲያደርግ አይታይም:: አሁን የተያዘው የትምህርት ጥራት ፓኬጁ ዲስኩርና ፋይዳው ከምርጫ 2002 ይዘል እንደሆነ የሚታይ ነው:: የአበባና የፎቁ ልማት ለብዙ ሰው የሥራ ዕድል መፍጠሩም ይታያል:: ሰቆቃችንን እየደበቀብን ተቸገርንና ነው እንጂ፤

ፎቁ የሌሎችም ቢሆን እኛም ለዓይናችን ደስ ይለናል። ፎቁም ሆነ አበባው ባለቤቱን ከመጥቀሙም ባሻገር ለመንግሥት የሚያስገኘው የውጭ ምንዛሪ፤ የግብርና የቀረጥ ትርፍ ግን ይበልጣል። በመሠረቱ የመንግሥት ትርፍ ማለት የሕዝብ ትርፍ ማለት አይደለም። የመንግሥት ገቢ መጨመር የሕዝብ ትርፍ የሚሆነው የሕዝብ መንግሥት ባለበት ሐገር ነው። ሁሉም የኢሕዴግ ለውጥ ተደምሮና ተቀንሶ የምናገኘው የመጨረሻ አጠቃላይ ውጤት ግን ድህነት አለመወገዱን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ እዲያውም ለከፋ የኑሮ ውድነት ተዳርጓል። እኛን፤ ትናንትናም ሆነ ዛሬ እጅግ እየበላን ያለውና በቅድሚያ እንዲታከክልንና እፎይታ እንድናገኝ የምንጓጓበት ዋናውና አጣዳፊው ችግራችን ያለው ሌላ ጋ እንጂ የአበባና የፎቅ ለውጦቹ ጋ አይደለም። በአጠቃላይ ሕዝብን ከድህነት ያላላቀቀ ለውጥ የነሱ እንጂ የኛ ለውጥ ሊሆን አይችልም። የበላንን የሚያክልን መንግሥትና ፖሊሲ ነው ፍላጎታችን። ፍጹም ድህው ሆነ ዝቅተኛና መካከለኛ ኑሮ የሚኖረው በብዙ 10 ሚሊዮኖች የሚቆጠረው ሕዝብ የብልጭልጩ የኢኮኖሚ ለውጥ ተጠቃሚ አይደለም። የጥቂት በዪዎች ተመልካች ነው የሆነው።

የኢሕአዴግ መንግሥት የሚመጻደቅበት የድህነት ማስወገጃ ፖሊሲው፤ የሚሊኒየም ልማት ግብና ስትራቴጂው በወረቀት ላይ የቀረ ከንቱ ህልም ሆኗል። በተግባር ታየ የሚባለው የኢኮኖሚ ለውጥ (ባለ ሁለት አሀዝ ዕድገት) ሕዝቡን አሁን ከሚገኝበት አስከፊና አዋራጅ የድህነት ኑሮው ሊያላቅቀው ያልቻለ ለውጥ ነው። የምግብ ዋስትናን እንኳ ለማረጋገጥ ያልቻለ የኢኮኖሚ ዕድገት ምን ዓይነትና የማን ዕድገት ነው? ሰብዓዊ ይዘትና ገጽታ የሌለው - የዜጎችን ኑሮ ያልለወጠና ያላሻሻለ ለውጥ ምን ዓይነትና የማን ለውጥ ነው? "የድህነት ማስወገጃ" ፖሊሲ፤ ግብ፤ ዒላማ፤ ስትራቴጂ የሚባለው ድህውን ከረሣና የማያይ ከሆነ፤ ሌሎችን ደግሞ የባሰ ድሀ የሚያደርግ ከሆነ ምኑ ላይ ነው "የድህነት ማስወገጃ" ምናምን የሚባለው? ከ19 ዓመታት የኢሕአዴግ መንግሥትነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን አተረፈ? የገቢና ወጪው ሂሳብ ሲወራረድ የሚታየው ዋናው ሥዕል የሕዝብ ኪሣራና ኪሣራ ነው። በአጭሩ በ19 ዓመት የግዛት ዘመኑ እንደፎከረው ዜጎቹን በቀን ሦስቴ መመገብ ይቅርና ለባሰ ድህነትና ረሀብ የዳረገ መንግሥት ምን ዓይነትና የማን መንግሥት ይሉታል? የኢኮኖሚ ብሶትና ተቃውሞውን ሊያሰማ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ለብቻው ሰልፍ ያደረገው ደፋሩ ኢትዮጵያዊ ወጣትም በራሱ መንገድ ያለው ይህንኑ ነው። እኔ በረሀብ አለንጋ እየተገረፍኩ ባለሁበት ሁኔታ 'ጮኦኦእክ" ብላችሁ የምትናገሩለት የፎቅ፤ የመንገድ፤ የመብራት፤ የአበባ የለውጥ ዜና 'አይይይሰማአአም'፤ ሊታየኝ አልቻለም - አይችልምም ነው ያለው። አንድ ነገር ታደርጉ እንደሆነ አድርጉ ነው ያለው።

እኛ እያየን ያለነው ግን የእኛና የእነርሱ ኑሮ የሰማይና ምድር ያህል እየተራራቀ መሄዱን ነው። ድህነት ለሚለው ቃል (ፅንሰሀሳብ) ዓለምም፤ ባለሙያዎቹም፤ እኛም ተራዎቹ ሰዎች ከምናውቀው የተለየ ትርጉም ሰጥተውት ይሆን እንዴ? ድህነት ማስወገድ ማለት የሥርዓቱና የባለሥልጣናት ወዳጅ፤ ዘመድና የጎጥ ልጅ የሆኑ የአየር ባየር ነጋዴዎችን ባንድ ጀንበር ሚሊዮኔር ማድረግ ነው? ሚሊዮኔር የነበሩ መሰሎቻቸውን በሙስና ባለብዙ ሚሊዮኔርና ቢሊዮኔር ማድረግ ይሆን? አለበለዚያ ለሕዝብ ጥቅምና ለልማት ዓላማ ስለመዋሉ አፋችንን ሞልተን የማንመሰክርለትን ግብር፤ ቀረጥና የውጭ ምንዛሪ ለመንግሥት የሚያስገኙ አዲስ የሐገር ውስጥና የውጭ ባለሐብቶችን መፍጠርና መንግሥታዊ ትርፍ ማጋበስ ድህነት ማስወገድ ሊሆን አይችልም። በፌዴራልም በክልልም ያሉ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናትን በየትልልቅ የፋይናንስና የንግድ ኩባንያዎች ውስጥ በቦርድ አባልነትም በዋና የንግድ ሸሪክነትም እያየን ነው። ከፓርቲ ንግድ ድርጅቶች ውጭም ማለት ነው። ይህ ይሆን እንዴ ድህነት ማስወገድ የሚባለው? አንዳንዶቹ ባለሥልጣኖች በሕገ ወጥ መንገድ አፍርተው የሚደብቁት ሐብት በቻይና ከተሞች በሚንደላቀቁ ልጆቻቸው በኩል ተበትኖ - ተበትኖም የሚያልቅ አይደለም፤ እንዲያውም የልጆቹ መጥፊያ ሳይሆን ይቀራል?

## "መልካም ገጽታን ማበላሸት"

ይህ ዘግናኝና መራር ሐቅ ሲገለጽ በኢኮኖሚው "ባለድሎች" ዘንድ ከጭፍን ጥላቻና ቅናት በመነጨ፤ መልካም ገጽታቸውን ለማበለሸት ወይም የፖለቲካ ትርፍን ለማግኘት ሲባል የቀረበ አሉባልታ አድርገው ያቀርቡታል። ዕውነትን፤ ምክርና ጥቆማን ማየትና መስማት የማይፈልግ ሥርዓት ምላሹ ሁልጊዜ ይኸው ነው። ለሌላው የሩቅ ተመልካች ደግሞ (ሐገር ውስጥም ሆኖ ሩቅ የሆነ ስንት አለ!) ይህ ሊሆን የማይችል ተራ ማጋነን እና ወሬ ማዳመቂያ መስሎ ይታየው ይሆናል። የምር በማስተዋልና በማሰላሰል ዋናውንና ትልቁን ሥዕል ለማየት የማይሞክሩ ሌሎች ደግሞ፤ ታዲያ አሁን ምን አዲስ ነገር መጣ? ድህነት ቀድሞም የነበረ አይደል እንዴ ይላሉ። ሁሉም የራሳቸው ጉዳይ!! በተለይ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ወገኖች ሩቅ በሆነ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ድንኳን

ውስጥ ስለሚኖሩ የጠኔውን ሐቅና የሕዝቡን ውርደትና መሸማቀቅ ለማየት ይችላሉ፤ ይፈልጋሉ ወይም ይጥራሉ ተብሎ አይጠበቅም:: ሐቁ ግን ክፍት አእምሮና ስስ ስሜት ባለው ተመልካች ሁሉ ቁልጭ ብሎ ሊታይ የሚችል ነው:: ይህ እኮ በደስታና በእርካታ የሚገልጹት መልካም ዜና አይደለም! በቃላት እየተራቀቁ የሚጽፉት የችሎታ ማሳያ ድርሰትም አይደለም:: በህሊና አስገዳጅነትና ለመፍትሔ መሻት ካልሆነ በስተቀር የራስን መዋረድ የሚያውጁበትን ይህን መሰሉን ሐቅ መግለጽ አይመችም:: ኩራትን የሚፈታተንና ስሜትን የሚተናነቅ ልብ ሰባሪ ነገር መሆኑን የሚያውቅ ያውቀዋል::

## ግን ሕዝቡ ኑሮውን እንዴት ቻለው?

ብዙ ሰዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እንዴት ነው ይህንን ኑሮ ችሎ እየኖረ ያለው? ብለው እንደየሁኔታው በማዘንም ግራ በመጋባትም ስሜት ውስጥ ሆነው ይጠይቃሉ:: ሕዝቡ በአስማት ነው የሚኖረው ወይስ እንዴት ነው ብለው የሚገረሙም ጥቂት አይደሉም::

> *አባዬ ትምህርት ቤት የሚቀርብ የአስማት ትርዒት ስላለ ለመግቢያ ሁለት ብር ብቻ ስጠኝ፤ ሌላ አላስቸግርህም፤ ብሎ ተማሪ ልጅ አባቱን ይለምናል:: አባት መለሰ የተባለውን ያልሰማ ይኖር ይሆን? ልጄ፤ ደግሞ አስማተኛ ለማየት ሩቅ መሄድና ገንዘብ መክፈል ምን ያስፈልጋል:: እኔ አስማተኛ አባትህ እዚሁ አለሁልህ አይደል፤ አታየኝም እንዴ በምን አይነት አስማት መላ ቤተሰቡን በ400 ብር ደሞዝ ከወር እስከ ወር እያኖርኩ እንዳለሁ::*

ይህ እዚህ የቀረበው ለፈገግታ አይደለም:: ሚስጥሩ አልታይ አልፈታ ሲል እውነትም አስማት ይሆን እንዴ ያስብላል ለማለት ነው:: ሚስጥሩ ግን በከፊል ቀደም ብሎ በጤፉ፤ በበርበሬውና በከሰሉ ጉዳይ ላይ እንደተገለጸው ነው:: በከፊል ደግሞ ወዲህ ነው:: ይህ ኢትዮጵያ ነው! የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥልቅና ጥብቅ የኃይማኖት ታሪክና ባህል ያለው ሕዝብ ነው:: አብዛኛውን ጊዜ የሆዱን ብሶትና በደሉን የሚያካፍለው፤ አቤት የሚለውና ለቅሶውን የሚያሰማው ለፈጣሪው በግልና እዚያው በደጁ ተገኝቶ ነው - ተመስገን የባሰ አታምጣብኝ ማለትን ሳይዘነጋ:: እና የኑሮውና የአኗኗሩ ሚስጥር በሩቅና በግዴለሽ ተመልካች ባይታይለት ለምን ይገርማል?

## ለሕዝቡ ብሶት የሚቀርብለት መንግሥታዊ ምላሽ - "አዲስ" የቅጣትና ሽልማት ሥርዓት

የኢትዮጵያ ሕዝብ የስቃይ ኑሮ ዛሬ ከምንጊዜውም በላይ ብሶበታል:: በምርጫ 97 ድምጹ ተዘርፏል:: ባልመረጠው መንግሥት ለመገዛት ተፈርዶበታል:: የዚህ ቀጥተኛ ውጤት የሆነው፤ የኑሮ ውድነቱ ብቻ ሣይሆን ዝርፊያው፤ የፖለቲካ ጭቆናና አፈናው፤ የሁሉም ዓይነት መብት ረገጣው፤ የዘር መድልዎውና የጎሣ ግጭቱ፤ ከሥራና መኖሪያ ማፈናቀሉና ሐገር ቆርሶ መሸጡ ሁሉም ከቀድሞው ብሷል::

በዚህ ሐገር፤ ዓለም የሚያውቀውና የሚሠራበት የሽልማትና የቅጣት ዓላማና ሥርዐቱ ሁሉ ተገለባብጧል:: ሊመሰገን፤ ሊሾም - ሊሸለም የሚገባው ይወገዛል፤ ይገለላል፤ ይቀጣል:: ሊገሰጽ፤ ሊታረም ካልሆነም ሊቀጣ የሚገባው ሰነፉ፤ አውደልዳዩ፤ ሠላዩና ጎሊናውን የሸጠው አድርባይ ደግሞ ልዩ ጥቅም ይሰጠዋል፤ ይሾማል፤ ይሸለማል:: ዋናው ነገር የደሞዝ ጥቅምና የደረጃ እድገት ብቻ የሚያስገኝ የትምህርት ማስረጃ ከየትም እንደምንም ብሎ ማቅረብና የታማኝነት ማረጋገጫ የሆነውን የኢሕአዴግ ፓርቲ ደብተር ይዞ መገኘት ነው:: በእምነትም በተግባርም እንደሚታየው፤ በዚህ ሥርዓት ቅድሚያ የሚሰጠው፤ ለሙያ ግዴታና ለሥራ ኃላፊነት ብቁ የሚያደርግ (በአንጻራዊነት) ጠንካራ ሥልጠና ለወሰደ፤ የተረጋገጠ የሥራ ብቃት፤ ቁርጠኝነትና ልምድ ይዞ ለተገኘ ባለሙያ/ሠራተኛ አይደለም:: በፍጹም:: እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱ ሠራተኛ የኢሕአዴግ አባልነት ፎርም ስላልሞላ ብቻ በሰበብ አስባቡ ተገፍቶ ከአገልግሎት ውጭ እየተደረገ ነው:: በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ ሰፍኖ የሚታየው በፖለቲካና በዘር መድልዎ ላይ የተመሠረተ የሽልማትና ቅጣት ሥርዓት ነው:: ይህንን አድሏዊ ሥርዓት ለመሸፋፈን እያገለገለ ያለው ደግሞ፤ ከአነዳደፉ ጀምሮ እስከ አፈጻጸሙ ድረስ ሆን ተብሎ እንዲዛባ የተደረገው "የሥራ ሂደት ማሻሻያ" - ቢፒአር የተባለው መርሐ ግብር ነው:: በዚህና በመሳሰለው ሰበብ ከሥራ የተንሳፈፈው፤ ከደረጃው ዝቅ የተደረገው ወይም የተፈናቀለው ዜጋ ቀጥሩ እጅግ ብዙ ነው::

ይህንን ተከትሎ የስንቱ ቤተሰብ ለባሰ ረሀብና ለጎዳና ተዳረገ? በዚህ የተነሳ ቤተሰባቸውን መመገብ ተስኗቸው በሀሳብና በሰቀቀን ብዛት እንደ እብደት ያደረጋቸው፤ መንገድ ላይ ለብቻቸው የሚያወሩና የሚሰሩትን ሳያውቁ ለተለያየ አደጋ የሚጋለጡትን ቤቱ ይቁጠራቸው:: በጣም የሚያሳቅቀው ደግሞ ችግራቸውን በቅጡ ካልተረዱ ልጆቻቸው ለሚቀርብላቸው ይህንን - ያንን አምጣ ለሚለው ጥያቄ የሚሰጡት መልስ መጥፋቱ ነው:: ዓይኑ እያየ ቤተሰቡ በረሀብ አለንጋ ከሚገረፍ ብሎ፤ ሁኔታውን ለመቀየርም ምንም አቅም ወይም ተስፋ ሲያጣ ቤተሰቡን ከቤት ትቶ የሚጠፋና የት እንደደረሰ እንኳ ሳይታወቅ የሚቀር ስንቱ ነው? ከዚህም በባሰ ይህ ጸሐፊ እንኳ ከአንድ ሁለት ወረዳ ብቻ በዚህ ምክንያት ራሳቸውን ያጠፉ የስድስት ሰዎችን አሳዛኝ ታሪክ (ከአንድ ራሱም በዚህ ስሜትና አዝማሚያ ውስጥ ከሚገኝ ሰለባ) ሰምቷል:: ሰዎቹ እርምጃውን ከመውሰዳቸው በፊት በየፊናቸው የተሰማቸውን ራስን የመጥላት፤ የመባባት፤ የማመንታትና የጥፋተኛነት ስሜት በትክክል ከራሳቸውና ከፈጣሪያቸው በቀር ማን ሊያውቅ ይችላል? የሰዎቹን ስሜትና እርምጃ ለመረዳት፤ "ይህ ዘግናኝ ግፍ የተፈጸመው በኔ ላይ ቢሆንስ ኖሮ፤ ይህ አስጨናቂ ምርጫና ውሳኔ የቀረበው ለኔ ቢሆንስ ኖሮ" ብሎ በጥልቅ ማሰላሰልን ይጠይቅ ይመስለኛል:: በዚህና በመሳሰለው ምሬት ወደ ውጭ ለመሰደድ ተገዶ ሐገሪቱ ያጣችውን ከፍተኛና ዝቅተኛ የባለሙያ / የሠራተኛ ኃይል ለጊዜ እንተወው:: በዚህ ሐገር በሰፈነው የፖለቲካና የዘር መድልዎ ምክንያት **ለማመን የሚቸግር ቁጥር ያለው የሰው ሐብት ከሐገር ግንባታ ሥራ ውጭ ተደርጎ በከንቱ እየባከነ ነው!!!** እጅግ ያስቆጫል!! እነርሱ እንደሆኑ ሁሉንም ነገር ቀደም ብለው ግልጽ አድርገውታል:: "የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣን ለመሾም ዋናው መስፈርታችን የግለሰቡ/ቧ ለሥርዓቱ ታማኝ ሆኖ መገኘት ብቻ ነው:: ሌላ ሌላው (የብቃት) መስፈርት ብዙም አያስጨንቀንም::" ብለዋል የሥርዓቱ ቁንጮ - ያውም በአደባባይ!

## የኢትዮጵያ ሕዝብ የለውጥ ፍላጎት

በአጠቃላይ መልካም ዜጋ ሊባል የሚገባው ወንድና ሴት ሁሉ፤ ማለትም ጠንካራው ገበሬ፤ ሠራተኛ፤ ነጋዴ፤ ወታደር፤ ተማሪና አስተማሪው፤ የኃይማኖት አገልጋዩ፤ ባለሙያው፤ ሕዝባዊው ምሑር፤ ፤ ሐገርና ወገን-ወዳዱ፤ ለአንድነት የቆመው፤ ፈሪሐ እግዚአብሔር ያለው፤ ለጎሊናው እንጂ ለሆዱ የማያድረው፤ ይሉኝታ የሚፈራው፤ ሰውና ሕግን የሚያከብረው ሐቀኛው ሁሉ፤ ይህ እንደወንጀል እየተቆጠረበት በመቀጣት ላይ ነው:: ሕዝቡ በገዛ ሐገሩ፤ በመኖሪያ ሠፈሩ፤ በሥራ ቦታው፤ በሙያው፤ በራሱና በልጆቹ ጉዳይ ሁሉ እንደማያገባው ነገር ባይተዋርና የዳር ተመልካች ተደርጓል:: ባልመረጡት መንግሥት መገዛት ማለት ይኸው አይደል:: በዚህ አሳፋሪ ምስል ፊት ነው "የሕዳሴውና የታላቅ ሐገር ግንባታው ራዕይ፤ ጥረትና ስኬት" ዲስኩር በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ዘወትር የሚለፈፈው:: የመሬቱ ላይ ተጨባጭ ሁኔታ የሚያረጋግጠው ግን ዕውነታው የዚህ ተቃራኒ መሆኑን ነው:: የሰውን (የዜጋን) ኑሮ ለመለወጥና ለዚህም በእጅ ያለን የሰው ኃብት በአግባቡ ለመጠቀም ግድ ያለው ሥርዓት ትናንትም አልነበረም፤ ዛሬም የለም:: የሕዝብ መንግሥት እስኪመጣም ድረስ አይኖርም:: ሕዝባዊ ሥርዓትና መንግሥት እስከምናመጣ ድረስም የተዛባው የሽልማትና ቅጣት ዓላማና ሥርዓቱ እንደጎመዘዘን ይቀጥላል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ዕውነት በጥልቅ በመረዳቱ፤ ከምርጫ 97ም እጅግ በሰፋና በሚያጣድፍ ሁኔታ የሥርዓት - የመንግሥት ለውጥ ይፈልጋል:: እነዚህ ሁሉ በርካታ አሳማኝ ምክንያቶች ባይጨመሩም ግን **የኢኮኖሚው ችግር፤ ድህነቱ፤ ረሃቡና መዋረዱ ብቻውን ለለውጥ ፈላጊነቱ ከበቂ በላይ ምክንያት ነው::** ይህ የኢኮኖሚ ችግር አጀንዳ ጎልቶ መውጣትና መታየት አለበት:: **በቀጣዩ ምርጫም ሆነ (ካለ) በቀጣዩ የለውጥ ትግል ከቀዳሚዎቹ አጀንዳዎች ተርታ መታየት ይኖርበታል::**

እርግጥ አሁን በተጨባጭ እንደሚታየው ከሆነ የመጪው ምርጫ ሂደት (የግንቦት 2002 ምርጫ) ሥዕል አሉታዊ ነው:: ይህ ሥዕል በአንዳች ተዓምር ተቀይሮ ምርጫው ውስጥ የሚገባ ከሆነ ይህን መሰሉን ሰው-ተኮርና ኑሮ-ተኮር የሆነ ውይይት ከወዲሁ ማካሄድ፤ ሃሳብን ማጥራትና ማስረጽ ፋይዳው እጅግ የላቀና ወቅታዊ ይመስለኛል:: **ይቀጥላል**